# ፀረ-ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 35 የካቲት15/ 30/2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገፆች


ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት የ2018 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ግምገማ ተካሄደ

ገጽ 2

የዲጂታል ቴክኖሎጂ ትግበራ የሙስና ተጋላጭነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና እየተጫወተ ይገኛል

ገጽ3

104 የፖሊስ አባላት በሥነምግባር ችግር ከሥራ ተሰናብተዋል

ገጽ 5

በዲሲፕሊን፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በመጠቀም ጤናማ፣ ግልጽና ከሙስና ነጻ የግብርና ጉምሩክ ሥርዓት እየተገነባ ነው።

ገጽ 6


**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!**

## ትውልዱን በዕውቀት እና ሥነ-ምግባር ማነጽ ይገባል - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ትውልዱ ለሀገር ብሩህ ተስፋ ሆኖ ዘላቂ ልማትን እንዲያረጋግጥ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጉታል፤ እነሱም ዕውቀት እና ሥነ-ምግባር ናቸው። ዕውቀት ትውልዱ ዓለምን እንዲረዳ፣ ችግሮችን በፈጠራ እንዲፈታና ቴክኖሎጂን እንዲያላምድ ብቃቱን ሲሰጠው፤ ሥነ-ምግባር ደግሞ ያገኘውን ዕውቀት ለወገኑና ለሀገሩ ጥቅም እንዲያውል፣ በቅንነትና በኃላፊነት ስሜት እንዲመራ ያደርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በወለጋ ቆይታቸው እንደ ጄነራል ታደሰ ብሩ እና አርቲስት አሊ ቢራ ሁሉ ለሁሉም ነገር "ትልቁ መፍትሔ ትምህርት ነው" የሚለውን መርህ በማስታወስ፤ ትውልዱን በዕውቀትና በሥነ-ምግባር በመቅረጽ የሀገርን ተስፋ ማለምለም እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ከዚህ አንፃር ወለጋ በታሪክ በሰለጠነ እና




በተማረ የሰው ኃይሏ የምትታወቅ መሆኗን ገልጸው፤ ወለጋ ለኢትዮጵያ እና ለአፍሪካ ታላላቅ ምሁራንን እና መሪዎችን ያበረከተች የጥበብ ማዕከል መሆኗን ተናግረዋል።

በተለይም እንደነ ኦኒሲሞስ ነሲብ፣ አስቴር ጋኖ፣ ጉዲና ቱምሳ፣ ባሮ ቱምሳ፣ አያና ብሩ፣ ኃይሌ ፊዳ እና ሳህሌ ደጋጎ ያሉ ታላላቅ ስብዕናዎች በሃይማኖት፣ በቴክኖሎጂ፣ በፖለቲካ እና በኪነ-ጥበብ ዘርፍ ያሳዩት ተምሳሌትነት ለሀገር ኩራት መሆኑን ጠቁመዋል። ከእነዚህም መካከል በቴክኖሎጂው ዘርፍ የታየው የታይፕራይተር ፈጠራ የአካባቢው ተወላጆች የነበራቸውን የፈጠራ አቅም የሚያሳይ ትልቅ ማሳያ መሆኑን አብራርተዋል። በአሁኑ ትውልድ ውስጥም እንደነዚህ ያሉ ባለራዕይ እና የለውጥ ሰዎች በብዛት እንዲፈጠሩ ማስቻል አስፈላጊ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል።



## ለኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እና ለፌደሬሽን ም/ቤት አመራሮችና አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለሁለቱም ምክር ቤቶች ከፍተኛ አመራሮችና አባላት በአራት የተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ለፀረ-ሙስና ትግል የአቅም ግንባታ ሥልጠና ሰጥቷል። ሥልጠናው ያተኮረባቸው ርዕሰ-ጉዳዮዎች የህዝብ ተወካዮዎች ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ሂደት፣ የህግ አስፈፃሚ አካላት ክትትልና ቁጥጥር ስራዎች፣ የምርጫ ክልል የህዝብ ውክልና ስራዎች፣ የዲፕሎማሲ ስራዎች እና የሙስና ስጋት ተጋላጭነት የሚሉ ናቸው። በሥልጠና መድረኩም የሁለቱም ም/ቤቶች ምክትል አፈጉባኤዎች፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና የኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሮች፣ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንደ ሀገር ሙስናን የሚጸየፍና መብቱን በገንዘብ የማይደራደር ዜጋ መፍጠር እንደሚገባ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ ገልጸዋል። ምክትል አፈጉባኤዋ በዘርፉ እየታዩ ያሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመቅረፍ በሥነ-ምግባር የተገነባና ሙስናን የሚጠየፍ ትውድል መፍጠር ይገባል ሲሉ አያይዘው አስገንዝበዋል። ሙስና እና ብልሹ አሰራርን አስፈፃሚው አካል እና ህግ አውጭው ለአንድ ዓላማ በጋራና በቅንጅት መስራት እንደሚጠበቅባቸውም አመላክተዋል።

ተቋማት ተልዕኳቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን ምክር ቤቶች በክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎቻቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው ምክትል አፈ ጉባኤዋ በተጨማሪ አሳስበዋል። ኮሚሽኑ የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት ሙስናን በመከላከል የሀገር ዕድገት ለማፋጠን በዘርፉ ምሁራን የቀረበው ጥናታዊ ሰነድ የሚበረታታ እና ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ገልጸዋል።

የሥልጠናውን አስፈላጊነት ያረጋገጡት የህዝብ ተወካዮዎች ም/ቤት ምክትል አፈጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ በምርጫ ዋዜማ ሁለቱንም ምክር ቤቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ ሥልጠና መዘጋጀቱና ይህ ዘርፍ እንዲህ ነው ብሎ በድፍረት መናገር ሙስናን ለመከላከል የመንግስትን የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል። ሥልጠናው በአገልግሎት አሰጣጥ እየታየ ያለውን ችግር የበለጠ እንድንታገል ያስችላል ብለዋል።

በተመሳሳይ የኢፌዴሪ የፌደሬሽን ም/ቤት ምክትል አፈገ-ባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ዘሀራ ኡመድ በበኩላቸው ምክር ቤታችን የዜጎች ፍትሀዊ የልማት ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ የሚበጀቱ በጀቶች









ያለምንም ልዩነት በቀመሩ መሰረት ይከፋፈላሉ ብለዋል፡ ፡ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚመነጩ በጀቶች ያለምንም ልዩነት ክፍፍል ማድረግ ብቻ ሳይሆን በጀቶች በትክክል ስራ ላይ ስለመዋላቸው እና የህዝቡን ፍላጎት ምን ያክል አርክተዋል የሚለውን ለማረጋገጥ ክትትልና ቁጥጥር የምናደርግበት አሰራር አለን ሲሉ አክለዋል።

ከፌደራል እስከ ክልል የተመደቡ በጀቶች ሳይሸራረፉ ስራ ላይ እንዲውሉና የህዝብን እኩል ተጠቃሚነት እንዲረጋግጡ ከሦሥቱም የመንግስታ አካላት ጋር ተናቦ መስራትን ስለሚጠይቅ ሁለቱም ምክር ቤቶች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጡ የበለጠ አቅም የሚፈጥር በመሆኑ ይህን የሥልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃችሁ አመራር አካላት ምስጋና ይገባችኋል ሲሉ አያይዘው ገልጸዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ስምምነት እና የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና መከላከያና መዋጊያ ስምምነት ፈራሚና አጽዳቂ እንደመሆኗ መጠን ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለሀገር እድገት ጠንቅ በመሆኑ ጥብቅ ህግ አውጥታለች ሲሉ የተከበሩ አቶ እውነቴ አለነ ገልጸዋል። ይሁን እንጂ በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ በኩል ያለው እንቅስቃሴ ደካማ በመሆኑ እስከአሁን ድረስ ያልተሻገርናቸው ችግሮቹ አሉ ብለዋል።

አያይዘውም የሙስና ወንጀልን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ብቻ መቀነስ ስለማይቻል በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ረገድ ሰፋፊ ስራዎችን መስራት ይገባል ብለዋል፤ የትውልድ ግንባታ ስራውም ሆነ ሙስና መከላከሉ ስራ በኮሚሽኑ ብቻ ስለማይሸፈን ሁሉም ሊረባረብ ይገባል ብለዋል።


ወደ ገጽ2 የዞረ ...

ከገጽ 1 የዞረ

የሥልጠና መድረኩን በንግግር የከፈቱት የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒኤችዲ) በበኩላቸው ሀገራችን ኢትዮጵያ በፀረ-ሙስና የትግል ጉዞ አለም አቀፍ ስምምነቶችን እና መርሆዎችን ተቀብላ የህግ አካል ከማድረግ ጀምሮ የፀረ-ሙስና ተቋማትን በማቋቋም የበኩሏን ጥረት እያደረገች ትገኛለች ብለዋል፡፡

ባለፉት 25 ዓመታት በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ፣ በሙስና መከላከል እና በህግ ማስከበር በኩል በርካታ ስራዎች ቢሰሩም ከሙስና ውስብስብነት ባህሪ አንጻር ውስንነቶች ነበሩ፤ ነር ግን በለውጡ ዘመን ተቋማዊና ሥርዓታዊ ሙስና እንዳይፈጸም መንግስት ቁርጠኛ አቋም ይዞ በመነሳቱ አመርቂ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ እንደ መንግስት ወደ ውጭ የሚሸሽ ሀብት እንደሌለ ያረጋገጥን ቢሆንም አሁንም በአንዳንድ ተቋማት የሚከሰቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች የአገልግሎት አሰጣጡን እየፈተኑት ይገኛሉ ብለዋል፡፡ ኮሚሽነሩ አክለውም የፀረ-ሙስና ትግሉ ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው የህግ አውጪው አካል ጉልህ ሚና እንዳለው እንገነዘባለን፤ ህግ አስፈጻሚው እና የዳኝነቱ አካል ግንኙነት ነጻ፣ ገለልተኛና ከጥቅም ግጭት የጸዳ መሆን እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡

አያይዘውም የሚወጡ ህጎች በጥናት ላይ የተመሰረቱና በብሔራዊ ጥቅም ላይ የማይደራደሩ ሆነው እንዲወጡ



የህግ አውጪው አካል ጠንከር ያለ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል ብለን እንደ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እናምናለን ያሉት ኮሚሽነሩ ይህን በተመለከተ ምክር ቤቶችም የሚመሩትን እያንዳንዱን ተቋም ሥነ-ምግባራዊ አድርጎ የመምራት ህጋዊና ሞራላዊ ግዴታ አለባቸው ብለዋል፡፡ የሥልጠናው ዓለማ ሙስና ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ ለመከላከል ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና የጋራ ግንዛቤ ለመውሰድ ነው፡፡ ሥልጠናውን ስናዘጋጅ ህጎችና ፖሊሲዎች ከመውጣታቸው በፊት በየደረጃው ያሉ የምክር ቤት አባላት ጋር መወያየቱ ጠቃሚ ነው ብለን ስለምናምን ነው ብለዋል፡፡ ይህ ተቋም ትውልዱን ከሥነምግባር ውድቀትና ከሙስና ተግባር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤ በዚህ ዓመት የትውልድ ሥነ-ምግባር



ግንባታ ስራዎቻችን ተደራሽ ለማድረግ ከ200 በላይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ለይተን የሥነ-ምግባር አምባሳደር አድርገን ተልዕኮ ሰጥተናቸዋል ብለዋል፡፡ ም/ኮሚሽነር ክቡር ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው ይህ መድረክ ለስራችን ወሳኝ ነው ብለን ያዘጋጀነው ስለሆነ ከመድረኩ የተገኙ ሃሳቦችን በግብዓትነት መውሰድ ጠቃሚ ነው ብለዋል፡፡ ህዝብን በታማኝነት የሚያገለግሉ እንዳሉ ሁሉ ጥቂቶች ደግሞ የሀቀኞቹን እምነት የሚሸረሽሩ አሉና እነሱን ማስተካከል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ አክለውም ለሙስና ምንጭ ትልቁና ዋናው ምክንያት ያመለካከት መበላሸት ነው ብሎ መውሰድ ይገባል፡፡ የአመላካከት ለውጥ እስካልመጣ ድረስ ሙsኛም፣ ሌባም ተባለ ዘራፊ ለውጥ የለውም፤ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ሁሉም የበኩሉን ሊወስድ እንደሚገባ ገልጸው፤ በተለይ ቋሚ ኮሚቴው በተቋማት እቅድና አፈጻጸም ላይ ትኩረት ሰጥቶ ግምገማና ቁጥጥር ቢያደረግ ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው በበኩላቸው ይህ የግንዛቤ መድረክ ሲዘጋጅ ህግ አውጪው አካል በፀረ-ሙስና ትግሉ ግንባር ቀደም ተዋናይ ሆኖ የመሪነት ሚናውን እንዲጫወት ለማስቻል ነው ብለዋል፡፡ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የመንገድ ፕሮጀክቶችን መከታተል ይኖረባቸዋል፤ የፓርላማ አባላትን አክብሮ አገልግሎት የማይሰጥ አመራር መኖር የለበትም፤ አንዳንድ የተቋማት መሪዎች ውስን ጨረታን በግዥ እቅዳቸው ውስጥ ሳያካትቱ መጨረሻ ላይ በውስን ጨረታ ግዥ ይፈፅማሉ ብለዋል፡፡ የንብረት አወጋገድ ሥርዓታችንም በመፈተሽ ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር ስራ መሰራት እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

የስልጠናው ተሳታፊ አንድ የም/ቤት አባል በበኩላቸው የሥልጠናውን አስፈላጊነት አንስተው፣እንደዚህ ዓይነት ሥልጠናዎች እስከታችኛው የምክር ቤት መዋቅር ድረስ በየጊዜው እየተሰጠ ግንዛቤ መፈጠር እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ ስልጠናው አመለካከትን ይቀይራል፣ መንግስታዊ ሙስና የለም የተባለው ትክክል ነው፤ ነገር ግን የትንንሽ ሙስና ተጋለጭነቱ ሥጋት አለ የሚለው ያስማማናል፡፡ ምክንያቱም በግለሰብ ደረጃ ሙስና እየተፈፀመ ነው፡፡ ለምሳሌ ከመሬት አስተዳደር፣ ከማዳበሪያ ግዥ፣ ከመዘጋጃ፣ ከፍርድ ቤትና ከገቢዎች ጋር በተያያዘ ሙስና እየተፈፀመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት የ2018 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ግምገማ ተካሄደ

በግምገማው የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር ክቡር ተመስገን ጡርነህ ባለፉት የለዉጥ ዓመታት የብልጽግና ዕሳቤ መሬት ነክቶ ፍሬ እያፈራ ነው ብለዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተቋማትና የተቋማት መሪዎች ግንባር ቀደም ተዋንያን ናቸው፡፡ የብልፅግና ጉዞ "እየሠራሁ ነው፤ ልሠራ ነበር፤ በመሥራት ላይ ነኝ"፤ የሚሉ ሪፖርቶችን አይቀበልም፡፡ ከተሠራ መታየት፤ ከተከናወነ መዳሰስ አለበት፡፡ በ2018 ዓ.ም የአዲስ ዓመት ዋዜማ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን አጠናቀን በጉባ ታላላቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን አብስረናል፡፡ የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት እንዲሁም የነዳጅ እና የማዳበሪያ ፋብሪካን ጨምሮ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ሜጋ ፕሮጀክቶችን ጀምረናል፡፡

መንግሥታችን ጀምሮ በፍጥነት መጨረስ መለያው ነው፤ በዚህ እሳቤ የተጠናቀቁትን ሸበሌ ሪዞርትንና አይሻ-2 የንፋስ ኃይል ማመንጫን አስመርቀናል፡፡ በቅርቡም የምናስመርቃቸው አሉ፡፡ መንገዶች፣ ድልድዮች፣ ግድቦች፣ ቤቶች፣ እየተገነቡ ናቸው፡፡ የጉባ ብሥራቶች ቀስ በቀስ ሥር ሰድደው ተግባራዊ እየሆኑ ናቸው፡፡ በግምገማችን የስራ እንቅስቃሴዎቻችንን እና ስኬቶቻችንን በልኩ መዝነናል፤ ድክመቶቻችንን ያለ ምሕረት ለማረም ተግባብተናል፤ የመፍትሔ መንገዶችን የሚያመላክት እና አዳዲስ ስልቶችን ለመንደፍ የሚያስችል ገንቢ ምክክር አድርገናል፡፡ ባለፉት ዓመታት እና በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ባስመዘገብነዉ ድል ሳንኩራራ ነገር ግን በልኩ እየተበረታታን በቀጣይ ስድስት ወራት ለላቀ ውጤትና ድል ለመትጋት ተግባብተናል ብለዋል፡፡

ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን በማፋጠን ሁሉም ተቋማት ወደ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲገቡ እየተሰራ መሆኑንም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ እና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር አለምፀሐይ ጳውሎስ ገልጸዋል፡፡ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ 14 ተቋማት የ2018 በጀት የግማሽ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ተገምግሟል፡፡ ሚኒስትሯ በግምገማ መድረኩ ተቋማት የኢትዮጵያን አጠቃላይ ሪፎርም በመምራት ለብልጽግና ጉዞ እና ዘላቂ ሀገራዊ ልማት እንዲሰሩ አስገንዝበዋል፡፡

ኢትዮጵያ የጀመረቻቸውን ዲጂታል 2030፣ የ5 ሚሊየን ኮደርስ ስልጠና፣ የፋይዳ ዲጂታል እና መሰል የሪፎርም ኢኒሼቲቮችን በታቀደው ልክ በመተግበር ለዘላቂ ብልጽግና መስራት ይገባል ብለዋል፡፡ የተጀመሩ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሳደግ እና ለብልጽግና ተደማሪ አቅም ለመፍጠር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት አርዓያ ሊሆኑ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ ለሌብነት እና ምዝበራ የተጋለጡ ተቋማት ላይ የዲጂታል አሰራርን በማጠናከር አገልግሎቶችን በልዩ ትኩረት በመምራትና ወደ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲገቡ በማድረግ እርካታን ማሳደግ እንደሚገባም አስረድተዋል፡፡

ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተጠሪ ተቋማት ከሆኑት መካከል የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አንዱ ሲሆን፤ በግምገማ መድረኩም የኮሚሽኑ አመራሮች እና የሥራ ኃላፊዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት እና ተጠሪ ተቋማት ከተውጣጡ 14 የፌዴራል ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች በክቡር ዶ/ር አክሊሉ ታደሰ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የሴክተሮችና አገራዊ ፕሮጀክቶች ክትትል ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ የተመራ ልዑክ ቡድን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን የሪፎርም የተከናወኑ ሥራዎችና ተቋማዊ ለውጡን በአካል በመገኘት ጎብኝተዋል፡፡







## ለዋና ኦዲተር ሠራተኞች የሥራ ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጠ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ለድጋፍ ዘርፍ የአስተዳደር ሠራተኞቹ በሥራ ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጥቷል፡፡ በቢሾፍቱ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በሁለት ዙር በተሰጠው ስልጠና የደንበኛ አገልግሎት መርሆች፣ መሰረታዊ የስራ ሥነ-ምግባር፣ የደንበኛ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትኩረት ባደረጉ ርዕሰ ጉዳዮች ያተኮረ ነው፡፡ የስልጠናው ዓላማም በዋናነት ሰራተኞች ሥራቸውን ሲያከናውኑ የደንበኛ አገልግሎት አሰጣጥን ተረድተው ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት እና የሙያ ሥነ-ምግባርን በመጠበቅ በአግባብ እንዲሰሩ አቅም ለመፍጠር ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ተገልጿል፡፡






## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ የሕዝብና የመንግሥት ሀብት ከምዝበራ መታደጉን አስታወቀ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የከተማዋን የ6 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፤ በሕግ የበላይነትን የማስከበር ሂደት 1 ሺህ 382 የፍርድ ቤት መዝገቦች ለአስተዳደሩ እንዲወሰኑ በማድረግ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የሕዝብና የመንግሥት ሀብት ከምዝበራ ማዳን የተቻለው የዐቃቤ ሕግን አቅም በማሳደግና በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ በተከናወኑ ጥብቅ የሪፎርም ሥራዎች ነው ብለዋል፡፡ በከተማዋ ሰላማዊ እንቅስቃሴን ለማረጋገጥና የከተማዋን ውበት ለመጠበቅ በተከናወነ የተቀናጀ ዘመቻ፤ ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራ፣ ሕገ-ወጥ ግንባታ፣ የጎዳና ላይ ንግድና ሕገ-ወጥ እርድን የመከላከል ተግባር በስፋት መከናወኑን ገልጸዋል፡፡

በዚህ የክትትል ሥራ 101 ቤቶች፣ 19 ሼዶች እና 178 ሔክታር መሬት ሕጋዊነታቸው ተረጋግጦ ወደ መንግሥት ንብረትነት መመለሳቸው ተነግሯል፡፡ የወንጀል ምጣኔን ከመቀነስ አኳያም ከሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያና የገንዘብ ዝውውር እንዲሁም ከዝርፊያ ጋር በተያያዘ በርካታ እርምጃዎች ተወስደዋል ብለዋል፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድም ግልጽ የቅሬታ ማቅረቢያ ሥርዓት በመዘርጋቱ፣ በብልሹ አሠራርና በሌብነት ተግባር ላይ የተሳተፉ 282 ሠራተኞች ላይ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃ መወሰዱ በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡





## 104 የፖሊስ አባላት በሥነምግባር ችግር ከሥራ ተሰናብተዋል - ፖሊስ

አዲስ አበባን የሚመጥን ዘመናዊና ታማኝ የፖሊስ ኃይል ለመፍጠር፣ ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው ለከተማው ምክር ቤት "የቤት ሥራዬን አከናውኛለሁ" የሚል ጠንካራ ሪፖርት አቅርበዋል። ፖሊስ የሕዝብ አለኝታ እንጂ ስጋት መሆን የለበትም በሚል መርህ፣ ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 104 የፖሊስ አባላት ከሥራ ተሰናብተዋል።

እነዚህ አባላት በተደጋጋሚ ምክርና ተግሣጽ ተሰጥቷቸው ሊታረሙ ያልቻሉ፣ በሥነ-ምግባር ብልሽትና በሰብዓዊ መብት ጥሰት እጃቸው የተገኘባቸው ናቸው። ኮሚሽነሩ "ከሕዝብ አገልግሎት በተቃራኒ የቆሙትን አንታገስም" የሚል ግልጽ መልእክት አስተላልፈዋል።





## በ100 ሚሊዮን ዶላር የሙስና ወንጀል የተሳተፉት የዩክሬን የቀድሞ የኢነርጂ ሚኒስትር ከአገር ለመውጣት ሲሞክሩ በቁጥጥር ስር ዋሉ

በ100 ሚሊዮን ዶላር የሙስና ወንጀል ከተሳተፉት ውስጥ አንዱ ናቸው የተባሉት የዩክሬን የቀድሞ የኢነርጂ ሚኒስትር ከአገር ለመውጣት ሲሞክሩ በቁጥጥር ስር መዋላቸው ተገልጿል። ባለፈው ዓመት በሙስና ቅሌት ስማቸው ከተጠቀሱት ባለሥልጣናት መካከል አንዱ የሆኑት እና በኋላ ላይ ከኃላፊነታቸው የተነሱት ጀርመን ጋሉሽቼንኮ፣ ዩክሬንን ለቅቀው ሲወጡ ባቡር ላይ መያዛቸው ተመላክቷል። በኅዳር ወር 100 ሚሊዮን ዶላር የዝርፊያ ወንጀል ውስጥ ከተሳተፉት በርካታ የመንግሥት ሰዎች አንዱ መሆናቸው ተጠቅሷል።

ይህ የሙስና ቅሌት የዩክሬን ፕሬዝዳንት ቮሎዲሚር ዜሌንስኪን አስተዳደር ይጥላል ተብሎ ተሰግቶ ነበር። የዜሌንስኪ አስተዳደር ወደ ሥልጣን የመጣው ሩሲያ ወረራ ከመፈጸሟ በፊት ሙስናን ከአገሪቱ ጠራርጎ ለማጥፋት ቃል በመግባት ነበር። ለዜሌንስኪ በጦርነቱ ወቅት የቅርብ አማካሪያቸው የነበሩት እና የጽህፈት ቤት ኃላፊው አንድሪ ይርማክ ቤታቸው ከተፈተሸ በኋላ ሥልጣናቸውን ለቅቀዋል። ፕሬዝዳንቱም ሆነ ይርማክ ጥፋት ሰርተዋል በሚል አልተከሰሱም። ይሁን እንጂ ይህ የሙስና ቅሌት ከተሰማ በኋላ በዩክሬን ሕገ መንግሥት መሠረት እ.አ.አ ከ2022 ጀምሮ በሩሲያ ወረራ ምክንያት ሳይካሄድ የቀረውን ምርጫ እንድታካሂድ ከአሜሪካ የሚደርሰውን ጫና በርትቷል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።



## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ም/ኃላፊን ጨምሮ 11 አመራር እና ሰራተኞች በፖሊስ ተይዘው ፍርድ ቤት ቀረቡ

የተጠረጠሩት አመራሮች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳዳር ቢሮ የቀድሞ ም/ኃላፊ፣ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የቀድሞ ኃላፊ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳዳር ቢሮ የቴክኒክ ጉዳይ ወሳኝ ባለሙያ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳዳር ቢሮ የቅሬታ እና አቤቱታ ባለሙያ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳዳር ቢሮ ይዞታ ማስተካከል ቡድን መሪ፣ የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቀድሞ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 መሬት ልማትና አስተዳደር የሰነድ አጣሪ ባለሙያ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳዳር ቢሮ ህግ/ቴክኒክ ጉዳይ ክትትል ዳይሬክተር፣ የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቴክኒክ ባለሙያ፣ የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቴክኒክ ባለሙያ እና በአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ የወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክተር የነበሩ በቁጥጥር ስር ውለው በፍርድ ቤት ለተጨማሪ ምርመራ የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆ ምርመራው ቀጥሏል።

ግለሰቦቹ ከግብር አበሮቻቸው ጋር በጥቅም ተመሳጥረው በህዝብና በመንግስት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ያለአግባብ በመጠቀም ተጠርጥረዋል። በዚህም በ2016 ዓ.ም በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ልዩ ቦታው አየር መንገድ አከባቢ የህዝብ እና የመንግስት ይዞታ የሆነውን በ9ኛው መዋቅራዊ ፕላን በዓድዋ ፓርክነት ተይዞ የነበረውን እና በ10ኛ መዋቅራዊ ፕላን በዊንዶው ኦፍ አፍሪካ ልዩ ልዩ የከተማዉ መተንፈሻ አረንጓዴ ስፍራ ፕሮጀክት በከተማ ደረጃ በመናፈሻነት ለህዝብ አገልግሎት የተያዘ እና በመሬት ባንክ ውስጥ ያለን ይዞታ ያለ ህጋዊ ምክንያት ሰነድ አልባ ይዞታ ነው በማለት ለዮርዳኖስ፣ ዘውዲቱ እና ጓደኞቻቸው የሲሚንቶ አከፋፋይ ህብረት ሽርክና ማህበር ለሚባሉት የቦታው ስፋት 2 ሺህ 905 ካ.ሜ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የቦታው ሊዝ ዋጋ 168 ሚሊየን 724 ሺህ 405 ብር የሚገመትን ጉዳት በማድረስ ከወረዳ፣ ክ/ከተማ እና መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ድረስ በጥቅም ተሳስረዉ ስልጣንን ያለ አግባብ በመገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ተጠርጥረዋል። በዚህም በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ቀርበው ተጨማሪ ጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸው ምርመራው ቀጥሏል።

## የድሆችን እርዳታ የሰረቀ ባለሙያ በቁጥጥር ስር ዋለ

በአዲስ አበባ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ውስጥ እጅግ አሳፋሪ የሆነ የሌብነት ድርጊት ተፈጽሟል። በክፍለ ከተማው የበጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ውስጥ የሚሰራ ባለሙያ (ሰራተኛ) ለችግረኞችና ለአቅመ ደካሞች ተብሎ ከተለያዩ ለጋሾች የተሰበሰቡ እቃዎችን ለግል ጥቅሙ ሲያስቀምጥ ተይዟል። በተለይም ከድሬደዋና ከሀዋሳ ተለግሰው የመጡ አልባሳትና ጫማዎችን መስረቁ ተገልጿል። ተጠርጣሪው በተቋሙ ሰው የማይኖርበት አሳቻ ሰዓት በመጠቀም ቁሳቁሶቹን በቦርሳ በመሙላት ወደ ቤቱ ለማጓጓዝ ሞክሯል። ነገር ግን በጥበቃ ሰራተኞችና በፖሊስ አባላት ንቁ ክትትል እጅ ከፍንጅ ተይዟል። የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ድርጊቱን በጽኑ አውግዟል። "በንፅህና ማገልገል ሲገባው ለችግረኞች የተሰበሰበን ሀብት መዝረፍ ህሊና ቢስነት ነው 'ብሏል። በአሁኑ ወቅት ተጠርጣሪው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሆኖ ምርመራ እየቀጠለ ነው፤ ተገቢውና አስተማሪ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድበት ይጠበቃል።



ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA


# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**


## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**

# ርዕሰ -አንቀፅ

## ዘርፎች በሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ ያላቸውን ቁልፍ ሚና በመረዳት መስራት አለባቸው!

የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናን ለመከላከል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ 27 ዘርፎች (Sectors) እንደ ዋና የትግል አጋር ይታያሉ። እነዚህ ዘርፎች በባህሪያቸው ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ወይም ከህዝብ ጋር ሰፊ ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው፣ በፀረ-ሙስና ስትራቴጂው ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። በዘርፎች ውስጥ የሚከናወኑ ዋና ዋና ሚናዎች በሚከተሉት ዐቢይ ነጥቦች ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

የሥነ-ምግባር መሠረተ-ልማትን መገንባት (Ethics Infrastructure):- እያንዳንዱ ዘርፍ በውስጡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍልን በማደራጀት የኮሚሽኑ ክንፍ ሆኖ ያገለግላል። መመሪያዎችን በማውጣት ለእያንዳንዱ ዘርፍ ልዩ ባህሪ የሚስማማ የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct) ያዘጋጃሉ። ክትትልና ቁጥጥር፣ የዘርፉ ሰራተኞች ከጥቅም ግጭት ነፃ መሆናቸውን እና የአሰራር ደንቦችን ማክበራቸውን በቅርብ ይከታተላሉ።

የአሰራር ስርዓት ማሻሻልና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም:- ሙስና የመከሰት እድሉ የሚጨምረው የተቋማት አሰራር ስርዓት ግልጽ ካልሆነና በሰው ንክኪ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ነው። አሰራርን ዲጂታይዝ ማድረግ በግብር አሰባሰብ፣ በንግድ ፍቃድ እና በመሬት አስተዳደር ዘርፎች ላይ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ ብልሹ አሰራርና ጉቦ እንዳይፈጠር ዕድሎችን ማጥበብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የአገልግሎት ስታንዳርድ በማውጣት አንድ አገልግሎት በስንት ቀናት እና በምን ያህል ወጪ መጠናቀቅ እንዳለበት ለህዝብ ግልጽ በማድረግ "ለአቋራጭ መንገድ" የሚገፋፉ ሁኔታዎችን ማስቀረት ተገቢ ነው።

የሀብት ምዝገባና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ:- ዘርፎች እና ተጠሪ ተቋማት በስራቸው ያሉ ተሿሚዎችና ባለሙያዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ የማመቻቸት ሚና አላቸው። ይህ አይነት ተግባር በመንግስትና ህዝብ ላይ ያለን አሰራር ግልጽነት ከመፍጠሩ ባሻገር ሁነኛ መተማመንን ይፈጥራል።

የግንዛቤ ማስጨበጥ እና የአመለካከት ለውጥ:- ዘርፎች "ሙስናን የማይሸከም ማህበረሰብ" የመፍጠር ሚና ይጫወታሉ። ለሰራተኞችና ለተገልጋዮች ስለ ሙስና አስከፊነትና ስለ ሥነምግብባር አስፈላጊነት ስልጠናዎችን በመስጠት የግንዛቤ ደራጃቸውን ከፍ ማድረግ ይችላሉ። ሰራተኞች ስለ ሙስና ያለምንም ስጋት ጥቆማ የሚሰጡበትን የጥበቃ ስርዓት ማመቻቸት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፦ አንዳንድ ዘርፎች ሙስና መከላከል ላይ ያላቸውን ልዩ ሚና ስናይ፣ የትምህርት ዘርፍ ተማሪዎች ሥነምግባር ግንባታ ላይ ከልጅነት ጀምሮ ታማኝነትን እና ሥነ-ምግባርን በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ማስረጽ ላይ መስራት ይገባቸዋል።

የፍትህ ዘርፍ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ በሙስና የተሳተፉ አካላት ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ፣ የመሬት አስተዳደር የመሬት አቅርቦት መረጃን ግልጽ በማድረግ በዘርፉ ያለውን ከፍተኛ የመዝረፍ ስጋት መቀነስ፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር የመንግስት ሀብት ለታለመለት አላማ ብቻ መዋሉን ማረጋገጥ አለባቸው። በአጠቃላይ በዘርፎች ሙስናን በመከላከል ላይ የተመሰረተ ስትራቴጂ ውጤታማ እንዲሆን በርብርብ መስራት ይገባቸዋል ። ኮሚሽኑ የስትራቴጅ አቅጣጫ ሲቀይስ፣ ዘርፎቹ ደግሞ ያንን አቅጣጫ ወደ ተግባር በመለወጥ ተቋማቸውን ከሙስና xeና ብልሹ አሰራሮችን የመከላከል ኃላፊነት እንዳለባቸው ተረድተው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

# ቆይታ

## በዲሲፕሊን፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በመጠቀም ጤናማ፣ ግልጽና ከሙስና ነጻ የግብርና ጉምሩክ ሥርዓት እየተገነባ ነው::

“ጤና ይስጥልኝ፤ ዛሬ በገቢዎች ሚኒስቴር ተገኝተናል:: የአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ጀርባ አጥንት የመንግስት ገቢ ሲሆን፣ ይህ የግብር፣ ታክስና ቀረጥ ገቢ በአግባቡ ተሰብስቦ ለሀገር እድገት እንዲውል ደግሞ በሥነ-ምግባር የታነጸ ሰራተኛ፣ ግልጽ አሰራር መዘርጋትና ከሙስና የጸዳ ተቋም መገንባት ወሳኝ ነው:: እንዲሁም የጉምሩክ ስርዓቱን ጤናማ ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባራትም ተመሳሳይ ናቸው::

ዛሬ በዚህ ዙሪያ ሰፊ ቆይታ የምናደርገው በገቢዎች ሚኒስቴር ተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከሆኑት ከአቶ ደጀኔ ደስታ ጋር ነው:: አቶ ደጀኔ፣ ስለመጡና ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በቅድሚያ እናመሰግናለን:: በተለይ እንደ ገቢዎች ዘርፍ (ገቢዎች ሚኒስቴርንና ጉምሩክ ኮሚሽንን አጠቃሎ) ሙስናን ለመከላከል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች፣ ስለ ሥነ-ምግባር ግንባታ ሥራዎች እና ስለ የአሰራር ግልጽነት ቆይታ አድርገናል:: መልካም ንባብ::”

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በገቢዎች ዘርፍ ውስጥ የሙስና ተጋላጭነትን ለመቀነስና ሰራተኞች በሥነ-ምግባር የታነጹ እንዲሆኑ ለማድረግ በዋናነት እየተተገበሩ ያሉት አሰራሮች ምን ምን ናቸው?

አቶ ደጀኔ ደስታ፡- እንደ ገቢዎች ዘርፍ ከምንሰራበት የስራ ባህሪ አንጻር ዘርፉ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ያለው ተጋላጭነት ሰፊ በመሆኑ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራን ነው:: ከዚህ አንጻር በመጀመሪያ በሥራ አካባቢ ያሉ የስጋት አካባቢዎችን እንለያለን:: በእያንዳንዱ አሰራር ውስጥ ያሉትን ስጋቶች በአግባቡ እንተነትናለን:: ስጋቶች እንዳይከሰቱ በቅድሚያ መሰራት ያለባቸውን ሥራዎች እንሰራለን:: ይህ ብቻ ሳይሆን በተለዩ የስጋት አካባቢዎች ሊከሰቱ በሚችሉ ችግሮች ወይም ብልሹ አሰራሮች ከመከሰታቸው አስቀድመን ችግሩ ያለበትን ደረጃ ለመለየትና አስቀድሞ ለመከላከል የአሰራር ሥርዓት ጥናቶችን እናደርጋለን:: የስጋት ደረጃ ካወጣን በኋላ ጥናቶችን እናከናውናለን:: ስልጠና የሚያስፈልግ ከሆነም በእነዚህ ስጋቶች ዙሪያ ሥልጠና ለመስጠት የራሳችን አቅምና ከሌሎች አካላት ጋር ተቋሙ በሚሰጠው ድጋፍ ጭምር ተጠቅመን እየሰጠን እንገኛለን:: ይህንንም በቀጣይ አጠናክረን የምንሰጠው ይሆናል::

ሌላው በሥነ-ምግባርና ሞራል እሴት ግንባታ ላይ ከፍተኛ የሀገር ባለውለታዎችንና ታዋቂ ሰዎችን የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ለሰራተኞቻችን የማነቃቂያና ግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ጭምር በማዘጋጀት ትልቅ ሥራ እየሰራን እንገኛለን:: ሌላው በዘርፋችን እየሰራን ያለነው በሥራ ላይ ሰራተኞቻችን አጥፍተው ሲገኙ አጥፊዎችን የሚጠይቀበት የሥነ-ምግባር ደንብ ያለን በመሆኑ አጥፊዎችን በሰራተኞች ዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት ጭምር ክስ በመመስረት እንደጥፋታቸው ልክ ተጠያቂ እንዲሆኑ እናደርጋለን:: የሚወሰደውም የዲሲፕሊን እርምጃ ከአነስተኛ የዲሲፕሊን ጥፋት እስከ ከፍተኛ ጥፋት እንደየጥፋት መጠን ከስራ እስከ ማሰናበት ድረስ አስጠይቀን አጥፊዎች ከዘርፉ እንዲወጡ ይደረጋል::

ይህንን እያደረግን ያለነው ዘርፉ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ በመሆኑና ጥፋቱ ሲከሰት በሀገርና በተገልጋይ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ስለሆነ ነው:: ወደ ዘርፉም የሚገቡ አዳዲስ ሰራተኞችም ዘርፉ ለብልሹ አሰራር ርህራሄ እንደሌለው አስቀድመው አውቀው እንዲገቡ አስቀድመን ስልጠና እንዲወስዱና ቃለ መሀላም ፈጽመው እንዲገቡ የቅርብ ክትትል እናደርጋለን:: ወንጀል ነክ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ደግሞ ወንጀልን የመመርመር ስልጣን ለተሰጠው የፖሊስ አካል እናስተላልፋለን:: በግልባጭም ለፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እናሳውቃለን:: ለፖሊስ ያስተላለፍናቸው ጉዳዮች የት እንደደረሱ በተቻለ መጠን ክትትል እናደርጋለን::

የሀብት ምዝገባን በተመለከተ፣ ገቢዎች ዘርፍ ሌሎች ተቋማት ሀብት ማስመዝገብን ሳይጀምሩ ለረጅም ዓመታት ሀብትን የማስመዝገብ ሥራ ከሰራተኛ ጀምሮ እስከ አመራሮች ድረስ ማስመዝገብ የረጅም ዓመታት ልምድ ያለው ዘርፍ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ተቋሙ ራሱ የሥነ-ምግባር ደንብ ቀርጾ ወደ ተግባር በመግባት ለረጅም ዓመታት እየሠራ ይገኛል:: ስለዚህ አጥፊዎች ተጠያቂ በሚሆኑበት ወቅት የሀብት ማመሳከሪያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለማመሳከሪያነት ለማዋል መረጃ እንጠይቃለን:: ከዚያ ባለፈ ባስመዘገቡት ሀብትና አለ ተብሎ በሚመጣ ጥቆማ መካከል አጠራጣሪ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ ሀብትን የማጣራት ስልጣን ለተሰጠው ለፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲያጣራና ውጤቱን እንዲያሳውቀን እናስተላልፋለን::

እኛ ወንጀል ነክ ጉዳዮችን አንመረምርም፤ የተጣሰ የሥነ-ምግባር ደንብ ካለ አጥፊዎቹን በሥነ-ምግባር ደንባችን መሰረት እንጠይቃለን፣ ከቃል ማስጠንቀቂያ እስከ ከፍተኛና ከሥራ ማሰናበት እርምጃ ድረስ እንዲወሰድባቸው አቅርበን እናስወስናለን:: በዚህ አይነት በበርካታ አጥፊዎች ላይ ህጋዊ የማስተካከያ ሥራ ተሰርቷል/እየተሰራ ይገኛል::


ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በ2018 ዓ.ም ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ሲከበር “የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ዘርፎች” በሚል እውቅናና ሽልማት አግኝታችኋል:: ለሌሎች ዘርፎች እንደ ተሞክሮ የሚወሰድ ምን ሰርታችኋል?

አቶ ደጀኔ ደስታ፡- ሥራዎቻችንን ስንሠራ ስራችን ለይድረስ ይድረስ ሳይሆን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሰራ ከልብ እንፈልጋለን:: ከኮሚሽኑ የሚወርዱትን መልእክቶች ሆነ አቅጣጫዎች ሁሉ አጉልተን ለመፈጸም ሳይሆን ሰፋ አድርገን ካለብን ችግር የበለጠ እንዲወጣ በማሰብ፣ የአመራር ብቻ አድረገን ሳይሆን መልእክቱ ሳይሸራረፍ እስከታች እንዲወርድ የተቻለንን ሁሉ ለማድረግ ጥረት እናደርጋለን:: ይህን እንደመነሻ በመውሰድ ሰፊ ሥራ ሰርተናል:: በዚህም መሰረት በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቻችን ጭምር በተመሳሳይ እለትና ሰዓት በአሉ በደመቀ ሁኔታ በከፍተኛ አመራሮች ጭምር በባለቤትነት ተይዞ ውጤታማ ስራ ሰርተናል::

ለሽልማትም የበቃነውና ውጤታማ ሆነናል ብዬ የማስበው አንዱና ዋናው ነገር በተቋማችን ውስጥ ያሉ የስራ ስጋት አካባቢዎችን ለይተን ማወቃችንና በሰነድ ጭምር ያዘጋጀን መሆናችን ነው:: ይህ ማለት ምን ማለት ነው? በተቋሙ ውስጥ ባሉ አሰራሮችና የሥራ ሂደቶች ውስጥ ያሉ ስጋቶች ምንድን ናቸው? የሚለውን ለመለየት በመጀመሪያ ደረጃ “ተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራር እና ሙስና መከላከል ስትራቴጂ” ነድፈናል:: በዚያ ስትራቴጂ ውስጥ እያንዳንዱን የሥራ ክፍል ዳሰስን:: እያንዳንዱን ክፍል ስንዳስስ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ክፍተት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሰራሮችን በሙሉ ለይተናል:: ጥናቶቻችንንም ሆነ ስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎቻችን ይህንን መነሻ ያደረገ ነው::

በሁለተኛ ደረጃ፣ የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥልጠና ሞጁል በጋራ እንድናዘጋጅ በሰጠን አቅጣጫ መሰረት እንደገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ 26 ተጋላጭ የስራ አካባቢዎችን በመለየት ስራ ሰርተናል:: በገቢዎችና በጉምሩክ ኮሚሽን ውስጥ እያንዳንዱ የሥራ ፍሰት ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑና ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት የመከላከያ ስትራቴጂ ነድፈናል:: እነዚህ ሥራዎችን መስራታችን ይመስለኛል ለሽልማቱ ያበቃን::

ሌላው ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት አስቀድመን ለመከላከል ትልቅ ጥረት እናደርጋለን:: አሁን እየሠራን ካለነው አንዱና ዋናው፤ በተቋሙ ውስጥ ለመቀጠር የሚመጡ ሰራተኞች በማንኛውም ጥፋት ከየትኛውም ተቋም የተሰናበቱ መሆን የለባቸውም:: በሥነ-ምግባራቸው አርዓያና ንጹህ ሰራተኞች መሆን አለባቸው ብለን እናምናለን:: ይህንን ለመለየት ቀደም ሲል አስቸጋሪ ስለነበር የራሳችንን የመረጃ ቋት (Database) እንዲለማልን ጥያቄ አቅርበን ስራው እየተገባደደ ይገኛል:: አሁን እየታየ ያለው ችግር፣ ከረጅም ዓመታት በፊት ከዘርፉ በብልሹ አሰራር የተሰናበቱ ሰዎች ሌላ ተቋም ተቀጥረው ከዚያ ተቋም የሥራ ልምድና ከሥነ-ምግባር ጉድለት ነጻ ደብዳቤ ይዘው ዳግም የሚገቡበት ሁኔታ እየተስተዋለ ይገኛል:: ሆኖም ግን ይህንን የሚያረጋግጥ ፍንጭ ስናገኝ መረጃውን በመተንተንና ተጨማሪ ማጣራት በማድረግ ከተቋሙ እንዲሰናበቱ እያደረግን እንገኛለን:: እንዲህ አይነቱን ጥፋት ለመከላከል በዘርፉ በሥነ-ምግባር ችግር የተሰናበቱ ሰራተኞችን መረጃ በሙሉ ዳታ ቤዝ ውስጥ እንዲቀመጥ ለማድረግ ቴክኖሎጂ እንደዲለማ ጠይቀን ተሰርቶ ሊጠናቀቅ እየተገባደደ ይገኛል::




ሌላው በገቢዎች ዘርፍ የሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮችንና ሙስናን ጥቆማ ለመስጠት የሚያስችል ቀለል ያለ የቴክኖሎጂ ሥርዓት እያለማን ሲሆን፤ በዚህ ዓመት ይጠናቀቃል:: እንደገቢዎች ዘርፍ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር ያለን ጠንካራ የስራ ትስስርና መናበቦች እጅግ ውጤታማ ነበሩ ብሎ መውሰድ ይቻላል:: የዘርፍ ሪፖርታችን አንድ ወር ያልተቆራረጠ የዘርፉ ተናቦ መስራት ውጤት ነበር:: ከክልሎች ጋር ያለንን የትስስር ስራ ለመጠናከር በከፍተኛ ተነሳሽነት እየሠራን እንገኛለን:: እንደገቢዎች ዘርፍ ከችግር ለመውጣት የምንችለው እንደዘርፍ ተናበን ስንሰራ ብቻ ነው የሚል ጽኑ እምነት ይዘን እየሠራን በመሆናችንና ከኮሚሽኑ የሚሰጡንን አቅጣጫዎች በመቀበል በወቅቱ ተግባራዊ ማድረጋችን ውጤታማ አድርጎናል ብዬ አስባለሁ::

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የገቢዎች ዘርፍ ከግብር ከፋዮች ጋር ከሚኖረው ግንኙነት ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ የሙስና እድሎችን (Corruption Risks) አስቀድሞ ለመለየትና ለመከላከል ምን ዓይነት የክትትል ሥርዓት ዘርግታችኋል? በሥነ-ምግባር ጥሰቶች (ጉቦ፣ የጥቅም ግጭት፣ ወዘተ) ላይ የሚታዩ ቅሬታዎች ምን ይመስላሉ? ምን ቅጣትስ ተወስዷል?

አቶ ደጀኔ ደስታ፡- አገልግሎት ለማግኘት የሚመጣ ግብር ከፋይ የሀገር ኩራትና የሀገር ባለቤት ጭምር ነው:: ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸው ሥራዎች ሰርተናል ያልናቸው በሙሉ ጤናማ የታክስ ሥርዓት ለመገንባት ከብልሹ አሰራር ነጻ የሆነ ለሁሉም እንደየጥያቄውና ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ያለምንም እጅ መንሻ ተገልጋይ አገልግሎቱን ማግኘት አለበት:: ይህ ሊሆን የሚችለው ታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤትም ሆነ ግብር ከፋዩ ወይም ደንበኛው ህግን አውቆና ለሚወጣ ታክስ ህግ ተገዢ ሆኖ የንግድ ስራውን ሲሰራ ብቻ ነው::

ዘርፉ በሁለት አጥፊዎች ማለትም ህገወጥ ነጋዴና በጉቦና እጅ መንሻ አገልግሎት በመስጠት የሚያንገላቱ በቁጥር ጥቂት የሆነ የታክስ ሰራተኞች እንዳሉ ይታመናል:: እነዚህ ሁለቱም አካላት በንግድ ሥርዓት ውስጥ እየተሹለከለኩ የሚሰሩ ነገር ግን የተቋሙ ገጽታ ላይ ጥላሸት የሚቀቡ አካላት ናቸው:: ጉቦ በሰጪና በተቀባይ መካከል የሚፈጸም አስነዋሪ ድርጊት ነው:: ጉቦ ሰጪ በህግ እንዲከፍል የሚጠበቅበትን ግብር/ቀረጥና ታክስ ከመክፈል ይልቅ በመደራደር ሊከፈል የሚገባውን ታክስ/ቀረጥ አሳንሶ ለመክፈል የእጅ መንሻ ለታክስ ሰራተኛ ከህግ ውጪ ይከፍላል:: ነገር ግን ከህግ ውጪ የሚጠየቅ ጥያቄ ካለ ግብር ከፋዩ ወይም ተገልጋዩ መረጃ ቢሰጥ ተጠያቂ ለማድረግ ዝግጁዎች ነን::

ከዚህ አንጻር ለግብር ከፋዩ በተለያዩ የውይይት መድረኮች ላይ ተገልጋዩ መብቱን በገንዘብ መግዛት እንደሌለበትና አጥፊዎችን አሳልፎ በመስጠት ድርሻውን እንዲወጣ ግንዛቤ እንፈጥራለን:: ግብር ከፋዩ ንጹህ አገልግሎት ማግኘት እንዳለበት፣ የሚያስቸግር ነገር ቢገጥም እንኳን በየደረጃው ላለ አመራር ከማሳወቅም ባሻገር እስከ ክቡራን ከፍተኛ አመራሮቻችን ድረስ ክፍት በሮች እንዳሉና ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችል እናሳውቃለን::

ሊያጋጥም የሚችል የሙስና እና ብልሹ ስራ ጥቆማቸውን በዋና መስሪያ ቤታችንም ሆነ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቻችን ለሚገኙ የሥነ-ምግባር የሥራ ክፍሎች ጥቆማቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ:: ይህንን አልፈው ጥፋት በሚፈጽሙት ላይ ደግሞ እርምጃ ይወሰዳል:: ለምሳሌ እንደገቢዎች ዘርፍ በዚህ ስድስት ወር ብቻ፡ በሥነ-ምግባር ጉድለት ከሥራ የተሰናበቱ 14፣ በደረጃ የተቀጡ 6፣ በደመወዝ የተቀጡ 35፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው 67፣ የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው 63፣ በከባድ ዲሲፕሊን ተከሰው በመታየት ላይ ያሉ 54፣ ለፌዴራል ፖሊስ የተላለፈ መረጃ 9፣ ጥቆማ ቀርቦባቸው በመጣራት ላይ ያሉ 5 ናቸው::

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- አሰራሮችን በቴክኖሎጂ በማዘመን (ዲጂታላይዝ በማድረግ) ረገድ የሚከናወኑ ሥራዎች በሰራተኞችና በደንበኞች መካከል ያለውን ቀጥተኛ ንክኪ በመቀነስ ረገድ ምን ውጤት እያመጡ ነው?

አቶ ደጀኔ ደስታ፡- የገቢዎች ሚኒስቴርም ሆነ ጉምሩክ ኮሚሽን ስራዎቻቸውን ከእጅ ንክኪ ነጻ የሆነ አሰራር ሥርዓት በከፍተኛ ደረጃ እየተገነቡ ይገኛሉ:: አስቀድመውም የጀመሩ ተቋማት ናቸው:: ከእጅ ንክኪ ነጻ የሆኑ ስራዎች በብዛት እየተሰሩ ሲሆን፤ ለምሳሌ የተለያዩ የክሊራንስ አገልግሎቶች አሁን በኦንላይን እየተሰጡ ነው:: ደረሰኝ በእጅ ስልክ የሚሰጥበት ሥርዓትም በመጠናቀቅ ላይ ነው:: ይህ ሲጠናቀቅ ማኑዋል ደረሰኝ ይቀራል፤ ማንኛውም ሰው የገዛውን እቃ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ደረሰኙ ወዲያውኑ ወደ ስልኩ ይላካል::

እንደ ጉምሩክ ኮሚሽን ደግሞ ከዋናው መስሪያ ቤት ሆኖ እስከ ሀገሪቱ ጠረፍ ያሉ ኬላዎችን መቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ስራ ላይ ውሏል፤ በእጅ ይደረግ የነበረው ፍተሻ በስካኒግ ማሽን ጭምር እንዲታገዝ ተደርጓል:: እንዲሁም ሌሎችም ስራዎች በዲጂታል ቴክኖሎጂ እየተቀየሩ ይገኛል:: ይህ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል::

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ብልሹ አሰራሮችን ለመቀነስ አንዱ መንገድ ፖሊሲ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የሥነ-ምግባር ስልጠናዎች ወይም የፖሊሲ ማሻሻያዎች ተደርገዋል?

አቶ ደጀኔ ደስታ፡- ሥራዎች ከማኑዋል ወደ ቴክኖሎጂ መሸጋገር አለባቸው የሚለው ራሱ አንዱ የፖሊሲ ሥራ ነው:: የግብር ከፋይ አገልግሎት አሰጣጥ በኤሌክትሮኒክስ መሆን አለበት የሚል ሀገራዊ አቅጣጫ ተይዞ እየተሠራ ነው:: ከጥቂት ዓመታት በኋላ የገቢዎችና ጉምሩክ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ብቻ ይሆናሉ::

ወደ ገጽ 6 የዞረ ...

## ቆይታ... ከገጽ 5 የዞረ

አሁን ባለ ሁኔታ እንኳን ብናይ ግብር ለመክፈል በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓትን በመጠቀም ግብር ከፋዩ ገንዘቡንና ጊዜውን ማዳን ችሏል ማለት ይቻላል:: ይህ በቂ ነው ማለት ሳይሆን በርካታ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ለመግለጽ ያክል ነው::

ዘርፉ በባህሪው ለሙስና ተጋላጭ ቢሆንም ይህንን ተጋላጭነት ለመከላከል ትልልቅ ሥራዎች እየተሠሩ ነው:: ነገር ግን አሁን እየተቸገርን ያለነው በዘርፉ ካለው እውነታ ማለትም ከሰርተው እጅግ ትላልቅ ሀገራዊ ስኬታማ ስራዎቻ ይልቅ ተጨባጭነታቸው ያልተረጋገጡ ወይም ማረጋገጫ ሊቀርብላቸው የማይችሉ ነገር ግን ደግሞ እዚህም እዚያም የሚወራው ወይም አጥፊዎችን አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ በሃሜት የተቋሙ ገጽታ ማጠልሸቱ በልጦ መገኘቱ ነው:: ህብረተሰቡ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ ጥቆማ ቢሰጠን አጥፊዎችን እንደየጥፋቱ ልክ ተጠያቂ ማድረግ እንችላለን:: “ገቢዎች እንዲህ አደረገ” ከሚባል ወሬ ይልቅ መረጃውን ይዞ የሚመጣ ሰው ያስፈልገናል::

ሀገራችንን የምንወድ ከሆነ እንዲህ አይነት ድርጊቶች ሲፈጸሙ መታገስ የለብንም:: አጥፊዎችን አሳልፎ ተሰጠቶን እኛ እርምጃ ካላስወሰድን ያኔ ተጠያቂ እንሆናለን:: እኛ ለአጥፊዎች ቦታ የለንም:: ይህንም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጭምር ከአሉባልታ ይልቅ ተጨባጭና በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን በአንክሮ ተናግረውታል:: የሀገር ባለቤቶች እንጂ እንደባእድ ዳር ቁመን ታዛቢዎች ልንሆን አይገባም:: ጥፋቶች ሊስተካከሉ የሚችሉት በሁሉም ትብብርና ቅንጅት እንዲሁም በሀገር ወዳድነትና በተቆርቋርነት ስንቆም ብቻ ነው::

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- ሰራተኞቻችሁንና አመራሮችን በሥነምግባራቸው ብቁ እንዲሆኑ ምን የሰራችሁት ሥራ አለ?

አቶ ደጀኔ ደስታ:- ዘንድሮ ውጤታማ ሥራ ሠርተናል፤ በተለይ አስቸጋሪና ውስብስብ የሥራ አካባቢዎችንና ተቋማዊ ስጋቶችን መለየት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሰራተኞች ግንዛቤ እንዲጨብጡ በማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ሥልጠና እንዲያገኙ አድርገናል:: እንዲሁም ከመሪዎችና ከቡድን አስተባባሪዎች ጀምሮ ብቁና ታማኝ መሪ እንዲሆኑ ከአፍሪካ ልህቀት ማዕከል ጋር በመተባበር ሥልጠና እንዲያገኙ አድርገናል:: አዳዲስ ሰራተኞች ሲቀጠሩም ልክ ለመደበኛ ስራ እንደሚሰጥ ስልጠና በሥነ-ምግባር ደንባችን ላይ ሥልጠና እንዲወስዱ አድርገናል::

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- ይህንን ጠንካራ ጎናችሁን ለማስቀጠል ምን አቅዳችኋል?

አቶ ደጀኔ ደስታ:- ባለፈው ዓመት ጥሩ ውጤት ብናመጣም መሥራት የምንችለውን ያክል አጠናቀን የመጨረሻ ጣሪያ ላይ አልደረስንም:: ሽልማቱ ሳይሆን ሥራው ነው የሚያስጨንቀን:: ሀገራችንን ከልመና ታሪክ ለማውጣትና በራሷ በጀት እንድትተዳደር በሚደረግ ጥረት ላይ የገቢዎች ዘርፍ የሥነ-ምግባር የሥራ ክፍላችን ላቅ ያለ ሚና ለመጫወት በተለይ ዘንድሮ በከፍተኛ ደረጃ ዝግጁ ነን:: በተለይ ከሥነ-ምግባርና ሞራል እሴት ግንባታ ላይ የሀገር ምልክት የሆኑ ግለሰቦችን በመጋበዝ ብዙ ስራ እንሰራለን::

ከተገልጋዩ ህብረተሰብ ጋርም በበለጠ ተቀራርበን መሥራት ላይ ትልቅ ትኩረት እንሰጣለን:: ከሁሉም በላይ በተቋም ገጽታ ግንባታ ላይ የህብረተሰቡን አሳታፊነት በማጠናከር ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመታገል በቁርጠኝነት እንሰራለን ብለን አስበናል:: ከፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር ያለንን ትስስር በከፍተኛ ደረጃ እናጠናክራለን፤ ከክልሎች ጋር የጀመርነውን ቅንጅታዊ ስራም በማጠናከር በዘርፉ የሚስተዋለውን መልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታት በቁርጠኝነት እንሰራለን::

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:- መጨረሻ ላይ የሚጨምሩት ነገር ካለ?

አቶ ደጀኔ ደስታ:- ኮሚሽኑ አቅሙን እያጠናከረና አቅጣጫዎችን እያስቀመጠ ውጤታማ እንድንሆን አድርጎናል:: የዘርፋችን አመራሮችም ሙስናንና ብልሹ አሰራርን አምርረው ለመታገል ሁሌም ድጋፋቸው ተለይቶን አያውቅምና ይህንን አጠናክረው እንዲቀጥሉ አደራ እላለሁ:: በዘርፉ ያለው ችግር ከወረዳ እስከ ፌዴራል ድረስ ትግሉን ማቀጣጠል ካልተቻለና ካልተፈታ ዘርፉ ጤናማ ይሆናል ብለን አናምንም፤ ስለዚህ ትስስራችንን እስከ ክልል ወረዳ ድረስ እናጠናክራለን:: ግብር ከፋዩ በንጹህ ህሊና ግብሩን ሊከፍል፣ ሰራተኛውም በንጹህ ህሊናና እጅ ሊያገለግል ይገባል:: እኛ የሥነ-ምግባር ሥራ ክፍሎች ዘብ የቆምነው




# ሳይቃጠል በቅጠል

## ሙስናን ለመታገል ህዝብና መንግስት በጋራ መቀናጀት አለባቸው!

እንደ ሀገር በየዘርፉ የሚፈፀሙ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ህዝብና መንግስት በመቀናጀት እጅና ጓንት ሆነው መስራት ይኖርባቸዋል:: ሙስና ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ በመከላከል ረገድ በትውልድ የሥነ-ምግባር ግንባታ ስራዎች ላይ ሰፋፊ ስራዎችን መስራት ከህዝብም፣ ከመንግስትም የሚጠበቅ ተግባር ነው:: በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የላቀ ትውልድ ማፍራት የሚያስችል የሰው ሀብት ልማት ላይ ያተኮሩ ፖሊሲና ስትራቴጅዎችን በሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት አንዱ የመንግስት ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል:: ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል በየደረጃው ላሉ የስራ መሪዎች ሰራተኞች እና ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማከናወን ደግሞ ሌላኛው ተግባሩ ነው::

ህዝብና መንግስት በቅንጅት መስራት አለባቸው ሲባል ሁለቱም አካላት ለአንድ ዓላማ በጋራ መቆም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ነው:: ከነዚህም ስራዎች አንዱ ህብረተሰቡን ያሳተፈ ግልፅና ገለልተኛ ህግ ከማውጣት ጀምሮ ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን በጥናት በመለየት የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ እና የመረጃ ተደራሽነትን ለህዝብ ማስፋት ያስፈልጋል:: ከመንግስት አካልም ሆነ ከማህበረሰብ በሥነ-ምግባራቸው የተሻሉና በስራቸው አርአያ የሆኑ ግለሰቦችን እውቅናና ማበረታቻ ሽማት መስጠት ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል መከተል ካለብን ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው::

በፀረ-ሙስና ትግል የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ሀገራትን አሰራርና ተሞክሮን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለትውልድ ማስተማሪያነት መጠቀም ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል መንግስት ሊከተለው የሚገባ ተግባር ነው:: እንዲሁም ለጥቅም ግጭት የሚዳርጉ አሰራሮችን በመፈተሽ ለሙስና የመጋለጥ እድላቸውን መቀነስ የሚያስችል አሰራር መቀየስ ያስፈልጋል:: ማህበረሰብ ከትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ እስከ መከላከል ድረስ ከመንግስት ያልተናነሰ ሀገራዊ ኃላፊነት አለበት::

ቤተሰብ ልጆች ሥነ-ምግባራዊ ሆነው በቅንነትና በታማኝነት ሀገርን ማገልገል የሚችሉ፣ ሙስናን የሚጠየፉ፣ መብታቸውን በገንዘብ የማይገዙ፣ በአቋራጭ ሳይሆን በላብና በወዝ ብቻ መለወጥና ማደግን ባህል አድርገው እንዲያድጉ በማድረግ መንግስትን ሊያግዙና ሊደግፉ ይገባል:: የሃይማኖት ተቋማትና ሌሎች የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች ለተከታዮቻቸው እምነቱ እና ድርጅቱ የሚፈቅደውን በጎ ስራ የዘወትር ተግባራቸው አድርገው እንዲንቀሳቀሱ ማስተማር ከቻሉ የሙስና ስጋት ይቀንሳል::

ማህበረሰቡ የመንግስት አገልግሎችን የሚያስተጓጉሉና በመልካም አስተዳደር ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ አካላትን ማጋለጥና ለመንግስት በማስረጃ ላይ የተመሰረተ መረጃ በመስጠት ሊተባበር ይገባል:: መንግስትም መረጃ ለሚሰጡ ዜጎች አስተማማኝ የደህንነት ዋስትና በመስጠት ህዝቡ ተባባሪ እንዲሆን መስራት ይኖርበታል::

ለፀረ-ሙስና ትግሉ ማስተማሩንም፣ መከላከሉንም ሆነ ህግ ማስከበሩን በአንድ ላይ አስተሳስሮ መስራት ከተቻለ እንደ ሀገር የሙስና ስጋትን በእጅጉ ለመቀነስ ያስችላል:: ሦሥቱም የመንግስት አካላት ንፁህ አሰራር መርህን እንዲከተሉ ማድረግ ያስፈልጋል:: ነፃና ገለልተኛ ተቋም መፍጠር የሚቻለው ህዝብና መንግስት ተቀናጅተውና ተናበው መስራት ሲችሉ ብቻ ነው:: የውጭ አገር ጉዞዎችና ሥጦታዎች ወዳጅነትን ለማፍራትና ተፅዕኖ ለመፍጠር ዓላማ ያላቸው ቢሆንም በውስጡ ድብቅ ፍላጎት ማስፈፀሚያነት ሚና ስለሚኖራቸው በብሄራዊ ጥቅምን አሳልፈው እንዳይሰጡ በጥንቃቄ መምራት ያስፈልጋል::

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ አምድ የተለያዩ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ በአገርዓቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑ በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የአገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት እና ግንዛቤ የሚፈጥሩ ዋና ዋና ጉዳዮች አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው።

በመሆኑም የአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሶሳ ከተማ የቀድሞ ም/ከንቲባ አቶ ንጋቱ ቂልጡ በሙስና ወንጀል በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል። በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የአሶሳ ከተማ ዐቃቤ ሕግ ተከሳሹን የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 13ን ጠቅሶ ክስ የመሰረተባቸው መሆኑ ይታወሳል። በዚህም ተከሳሹ ስልጣንን ያለአግባብ በመገልገል በተለያዩ ጊዜያት ከሕግ አግባብ ውጪ የተለያየ መጠን ያላቸው ይዞታዎችን በልጃቸው ስምና ለተለያዩ ግለሰቦች ስም እንዲሰጥ አድርገዋል በሚል ተከሰው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሲታይ ቆይቷል። የአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን መርምሮ በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም፣ ተከሳሹ መከላከል ባለመቻላቸው የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፎባቸዋል።

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኝ የቅጣት አስተያየት መርምሮ ተከሳሹን በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ4 ሺህ 500 ብር እንዲቀጡ ውሳኔ አስተላልፏል። በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ በሕገ ወጥ መንገድ በተከሳሹ የተወሰዱ ይዞታ ማረጋገጫዎች እንዲመክኑ እና ይዞታው ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥቷል።



በሌላ የሙስና መረጃ በሐሰተኛ የባንክ ዋስትና ሰነድ እና በሌሎች ሐሰተኛ ሰነዶች በመጠቀም ህገወጥ የጥቅም ትስስር በመፍጠር የባንክ አሰራርና ሕግን ባልተከተለ መልኩ በገዳ ባንክ፣ በኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በሌሎች ድርጅቶች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል በመፈፀም ከ89 ሚሊዮን 296 ሺህ ብር በላይ ጉዳት አድርሶ በሕግ ሲፈለግ የነበረውን ተጠርጣሪ ከነግብረ-አበሮቹ በቁጥጥር ሥር አውሎ ምርመራ እያጣራ መሆኑን የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ አስታውቋል፡ ፡ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንደሚያስረዳው ተጠርጣሪዎቹ ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀምና ሐሰተኛ የባንክ የዋስትና ሰነዶችን በማዘጋጀት የወንጀል ድርጊቱን የፈጸሙ ሲሆን፤ በተለይም የጎደር ዋይን ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ ዋነኛው ተጠርጣሪ ጌታሁን መለስ ልይህ ከገዳ ባንክ አገምሳ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ አብዲሳ ቶሎሳ ደበሌ ጋር በጥቅም በመመሳጠር፤ የቅርንጫፉን የሥራ ኃላፊ ፊርማና ማኅተም በመጠቀም ለወንጀል ድርጊታቸው ማስፈጸሚያነት ሲገለገሉ መቆየታቸውን ፖሊስ በምርመራው አረጋግጧል።

ተጠርጣሪዎቹ በዚህ የተቀነባበረ የወንጀል ድርጊት ለወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ሕብረት ሥራ ዩኒየን የውል ማስከበሪያና የቅድመ ክፍያ ዋስትና በማስመሰል 23 ሚሊዮን 296 ሺህ ብር እንዲሁም ለፈናን መሃመድ በሽር የቀለም ማምረቻ ድርጅት የ20 ሚሊዮን ብር የሐሰት የዱቤ ሽያጭ ዋስትና ሰነድ በማቅረብ፣ በድምሩ 43 ሚሊየን 296 ሺህ ብር የገንዘብ ጉዳት እንዲደርስ ማድረጋቸውን የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ያመላክታል። አበባው መኮንን አረጉ የተባለ ሌላኛው ተጠርጣሪ ከጌታሁን መለስ ልይህ እና ከአብዲሳ ቶሎሳ ደበሌ የተባሉት ተጠርጣሪዎች ከባድ የሙስና ወንጀሉን እንዲፈጽሙ ሁኔታዎችን ያመቻቸ፤ ያግባባና ያገናኘ ሲሆን፣ ጌታሁን መለስ ልይህ በቁጥጥር ስር እስከዋለበት ቀን ድረስ በበላይነት ወንጀሉ እንዲፈፀም ትልቅ ተሳትፎና ከፍተኛ የጥቅም ትስስር የነበረው መሆኑን ፖሊስ በምርመራው አረጋግጧል።

# መልካም ዜጋ

## የመኩሪያነት ሰንደቅ የዋና ኢንስፔክተር አደፍርስ ታፈሰ ታማኝነትና የህሊና ዳኝነት

በጥቅም በማይደለል ማንነት፣ በቅንነት እና በሙያ ሥነ-ምግባር የታነጹት ዋና ኢንስፔክተር አደፍርስ ታፈሰ፤ በደሴ ከተማ ጎዳናዎች ላይ የፖሊስነትን ክብር ከፍ የሚያደርግ ደማቅ አርአያነት አሳይተዋል። በደሴ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ የትራፊክ አደጋ መከላከልና ቁጥጥር ክፍል ኃላፊ የሆኑት ዋና ኢንስፔክተር አደፍርስ፣ ጥር 28 ቀን 2018 ዓ.ም በመደበኛ የሥራ ተግባራቸው ላይ እያሉ ነበር ድንገት በጎዳና ላይ የወደቀ 25,400 (ሃያ አምስት ሺህ አራት መቶ) ብር ያገኙት።መኮንኑ ያገኙትን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው ከማዋል ይልቅ፣ ለለበሱት የፖሊስ ዩኒፎርም ክብርና ለህዝብ አደራ በመገዛት ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል በማስረከብ የታማኝነት ተምሳሌት መሆናቸውን አስመስክረዋል።

ይህ ድርጊት ከገንዘብ ዝውውር ባለፈ ፖሊስ የገባውን ህዝብን በታማኝነት እና በኃላፊነት የማገልገል ቃልኪዳን



የሚያሳይ ተግባር ፈጽመዋል። የተቋሙን ክብር ከፍ ማድረግና የደሴ ከተማ ፖሊስ መምሪያን ስም በህዝብ ዘንድ ይበልጥ ጎልቶ እንዲታይ አድርገዋል። ፖሊስ የህዝብ አለኝታና የታማኝነት ምንጭ መሆኑን በተግባር አሳይተዋል። መኮነኑ የፈጸሙት በጎ ተግባር ለሌሎች የፖሊስ አባላትና አመራሮች የሞራል ልዕልና ከምንም በላይ መሆኑን ትልቅ ትምህርት ሰጥተዋል።

”የለበስኩት ዩኒፎርም የህዝብ አደራ ነው‘ የሚለውን መርህ በተግባር ያሳዩት ዋና ኢንስፔክተር አደፍርስ፣ በዘመናዊ የፖሊስ አገልግሎት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ታማኝ ተልዕኮ ፈፃሚነት በግልጽ አሳይተዋል። የዋና ኢንስፔክተር አደፍርስ ታፈሰ ታማኝነት በቁሳቁስ በናወዘ ዓለም ውስጥ የሞራል ልዕልና ምን ማለት እንደሆነ በትልቅ ድምፅ ያስተማረ ክስተት በመሆኑ ክብር ይገባዎታል። በሌላ የመልካም ተምሳሌት መረጃ በምዕራብ ጎጃም ዞን ሰከላ ወረዳ ግሽ ዓባይ ከተማ የሚኖር የ27 ዓመቱ ወጣት ዳንኤል ታደለ በባንክ አካውንቱ ላይ በስህተት የተላከለትን 930,000 (ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሺህ) ብር ሙሉ በሙሉ ለባለቤቱ መመለሱ ተገልጿል። ወጣቱ በግ በማድለብ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ታታሪ ዜጋ ነው። ገንዘቡ ከድሬዳዋ ከተማ በጋዲሣ ገነቴ ሁነዴ ተብሎ ከተጠራው ግለሰብ በስህተት ወደ አካውንቱ መግባቱን ሲያውቅ፣ ያለ ማንኛውም ጫና ወይም ዛቻ ተጽእኖ ሳይደርስበት ገንዘቡን በትክክለኛው ትራንዛክሽን መንገድ አምስት ሳንቲም ሳያጎድል መልሷል። ዳንኤል ሲገልጽ የቄሣርን ለቄሣር በሚል መርህ እንደምኖር ነው። የሰው ላብ ያላወጣበትን ገንዘብ መብላት ባህላችንና እምነታችን አይፈቅድም። የሰው ገንዘብ መውሰድ እምነትን ያጎድላል፣ እድሜና ጤናም አይሆንም። ጫና ቢደርስበትም ሳይረበሽ በህሊናው ደስተኛ ሆኖ ተግባሩን አጠናቋል።ምንም እንኳን ባለቤቱ በተገቢው አመሰግኖት ባይገልጽም፣ ዳንኤል ህሊናው በማረፉ ደስተኛ መሆኑን ገልጿል።





COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA

Account to Account Transfer

Branch: FELEGE GHION BRANCH
Date: 05/02/26
Tran Ref: FT26036WZ67V
Dr.AcctNo:1000524339289
Acct Name:DANIEL TADELE KASSAHUN
Debit Amt.ETB 930,000.00
Cal.Rate:
Charge/Comm ETB55.00
VAT (15%) ETB8.25
Total Debit ETB930063.25
Cr.AcctNo:1000417110201
Acct Name:GADISA GENETI HUNDE
Credit.Amt: ETB930000.00
Orderd By:
Narrative:
User ID:

# ኪነ-ጥበብ

## “የአህያ ሌባ ከኪሱ ቅቤ አያጣም”

በእኛ ማህበረሰብ ውስጥ ከአህያ ሌባ ጋር በተያያዘ ለረጅም ዘመናት የሚነገር ጥንታዊ ምሳሌ አለ፡፡ ይህም የአህያ “የአህያ ሌባ ከኪሱ ቅቤ አያጣም” የሚል ነው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሩ ያለምንም ኮሽታ በረቀቀ ሁኔታ የሚፈጸም የስርቆት ወንጀልን ለመግለጽ ታስቦ የሚነገር ነው፡፡ የአህያ ሌባ ለምንድን ነው በኪሱ ቅቤ የሚይዘው? ለመሆኑ የአህያ ሌባ እና ቅቤ ምን ግንኙነት አላቸው? አህያ ሆዱ ከሞላና ከጋጣው ሲወጣ የማናፋት/የመጮህ ልማድ አለው፡፡ የሚጮህ እንስሳ መስረቅ ደግሞ አስቸጋሪ ነው፡፡ በመጮሁ ሌባውን ለአደጋ ሊያጋልጠው ይችላል፡፡ አህያ ያንን ኃይለኛ ድምጽ ማውጣት የሚችለው ፊንጢጣውን ወደ ሆዱ በኃይል ሲወጣ ወይም ሲያጠልቅ ብቻ ነው፡፡ በፊንጢጣ መወጠር አፍ ይከፈታል፡፡ ያ ካልሆነ ድምጽ አይወጣም፡፡

ይህንን ጠንቅቆ የሚያውቀው የአህያ ሌባ ጋጣ (የአህያ ማደሪያ) ገልብጦ ከገባ በኋላ የሥራው መጀመሪያ የሚያደርገው የአህያውን ፊንጢጣ በቅቤ መቀባት ነው፡፡ ቅቤን እንደ ማለስለሻ (lu-bricant) ይጠቀምበታል፡፡ ከዚያም አህያውን የልማዱን ለማድረስ ቢጮህም ሥርዓቱ ተዛብቷልና ፊንጢጣው መወጠር አይችልም፤ አፍም መከፈት አይችልም፡፡ በዚህም ያለምንም ሥጋት አህያውን እየነዳ ወደ ፈለገው ቦታ ያደርሳል፡፡

በዚህ ዘመን ያሉ ሙሰኞችም የአህያ ሌባውን ገጸ ባህሪይ የተላበሱ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሙስናን ለመፈጸም የረቀቁ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ለሚፈጽሙት የሙስና ወንጀል እንዳይነቃ ማስታገሻ ዘዴ አስቀድመው ያዘጋጃሉ፡፡ ሙስና ሲፈጸም የሚመለከቱ ሰዎች እንዳይጮሁ በጥቅማጥቅም አፋቸውን ያዘጋሉ፡፡ ከኅሊናቸው ተሟግተው ለመጠቆም ቢፈልጉ እንኳ የተቀቡት የሙስና ማለስለሻ (lubricant) አቅም ያሳጣቸዋል፡፡ ሙሰኞች የዘረፉት ሀብት እንዳይታወቅ መረጃ ይሰውራሉ፣ ያቃጥላሉ፣ አቋም ያለውን እና ቢነቃብኝ ያስይዘኛል ብለው የጠረጠሩትን ደግሞ ቀርበው ቅቤ መቀባት ስለማይችሉ ከመንገዳቸው ያስወግዳሉ፡፡

የአህያ ሌባና የቅቤ ጉዳይን ዛሬ በሙስና አውድ ውስጥ ስንመለከተው በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሙስናው በሌሊት ይሰራል፤ ማለትም በስውር ሰው ሳያይ፣ ሳይሰማና ሳይታወቅ በቢሮዎች ውስጥ በውል ላይ በጨረታ፣ በቀጠሮ፣ ፍርድ ቤት እና በመሳሰሉት ተቋማት ውስጥ ይከናወናል፡፡ የአህያው ጩኸት ወንጀል መፈጸሙን የሚያውቅ፣ የሚጠቁም፣ የሚመሰክር ሰው ወይም ምስክር፣ ሰራተኛ፣ ባለስልጣን፣ የህዝብ አባል፣ ተቃዋሚ፣ ጋዜጠኛ እና የሚመለከታቸው አካላት ናቸው፡፡ ቅቤው ወንጀሉን የሚያውቁ ሰዎች ወንጀሉን እንዳይጠቁሙ ማለዘቢያ ስጦታ፣ ጥቅም፣ ቦታ፣ ጥበቃ፣ ደህንነት ወይም ማስፈራሪያ ነው፡፡ ይህን ቅቤ ሲቀባላቸው (ሲሰጣቸው) ድምጻቸው ይዘጋል፤ መጮህ፣ መቃወም፣ መግለጽ፣ መናገር አይችሉም ዝም ይላሉ፡፡

ሙሰኞች ሌሎችን በማፈን ወይም የጥቅም ተጋሪ በማድረግ የዘረፉትን ሀብት ያሸሻሉ፡፡ ሙሰኛው የተፈጸመው ገንዘብ፣ መብት፣ ንብረት፣ ዕድል… በስውር ይወሰዳል፡፡ ህዝቡ ግን አያውቀውም፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች  እኔ አውቃለሁ፤  እያየሁ ነው ይላሉ፡፡ ግን ሲጠየቁ  አይደለም፣ አላየሁም፣ አላውቅም ይላሉ፡፡ ለምን?  ምክንያቱ ቅቤ ተቀብቶባቸዋልና፡፡ ቅቤው አንዳንድ ጊዜ ትንሽ ገንዘብ ነው፤ አንዳንድ ጊዜ ትልቅ ቦታ ነው፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ 0 ዝም ብለህ ተቀመጥ ካልሆነ  የሚል ማስፈራሪያ ነው፡፡

መፍትሄው ምን ይሆን? ሙሰኞች ዝም እንድንል አደርገው የሚዘርፉትና የሚነጥቁት የበሽተኞችን ህይወት፣ የድሆችን ጉሮሮ እና የነገ የልጆቻንን ተስፋ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ  ሙስና እንዳንጮህ፣ እንዳንናገር ከሚከለክለን ሙሰኞች በኪሳቸው ይዘው ከሚዞሩት የመደለያ ቅቤ ራሳችንን እንጠበቅ፡፡ የአህያ ሌባና ሙሰኛ የመጨረሻ ምእራፉ የሚጠናቀቀው በውርደት ነው፡፡